# Summer RISE 2020 Student Agreement
# ሠመር ራይዝ 2020 የተማሪ ስምምነት

Partnerships Unit
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
45 West Gude Drive, Room 2301, Rockville, Maryland 20850
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ-የአጋርነት ክፍል

## PARENT/GUARDIAN/ELIGIBLE STUDENT CONSENT ወላጅ/ሞግዚት/ብቃት ያለው-ያላት ተማሪ ስምምነት

ሠመር ራይዝ 2020 ፕሮግራም የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚማሩ ራይዚንግ ጁንየሮች እና ለሲንየሮች በሠመር 2020 የሙያዊ ትምህርት እድሎችን ለመስጠት ነው። ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ስመዘገብ፣ በ 2020-2021 የትምህርት ዓመት በ MCPS 11ኛ ክፍል ጁንየር ተማሪ ወይም 12ኛ ክፍል ሲንየር ተማሪ ስለምሆን ብቁ እንደሆንኩ በማረጋገጥ ነው። በሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ስሳተፍ ከወላጅ/ሞግዚት ጋር በአንድነት ሙሉ ኃላፊነት ወስጄ ነው።

1. ተረድቻለሁ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ተሳታፊ እንደመሆኔ መጠን፣ በሣምንት ከ15 እስከ 20 ሠዓት እና በቀን ከ8 ሠዓት የማይበልጥ፣ በሣምንት ከ30 ሠዓት የማይበልጥ፣ በጠቅላላዉ ከ60 እስከ 80 ሠአት ከ3 እስከ 4 ሣምንታት በሙያዊ ልምድ በምሳተፍበት ጣቢያ ("Career Experience") በእጅ የሚሠሩ በሙያዊ የትምህርት እድሎች ላይ በመሣተፍ አስፈላጊውን ጊዜ እንደማሳልፍ። ጁላይ 6/2020 ተጀምሮ ጁላይ 31/2020 የሚጠናቀቀው የሥራ ልምድ የማግኘት ሥራ በሣምንት እስከ አምስት ቀናት፣ ከሦስት እስከ አራት ሣምንቶችን ሊወስድ ይችላል።
2. ተገንዝቤአለሁ ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ከመመዝገቤ በፊት ለሙያ ሥራ ልምድ ምደባ ለሠመር ራይዝ ቡድን እንዲያመች የራሴን ሦስት ዋና ዋና የሙያ ምርጫዎቼን ለይቶ ለማወቅ በ Naviance የሚሰጠውን "the Career Interest Profiler እና the Career Cluster Finder" መውሰድ እንዳለብኝ።
3. ተገንዝቤአለሁ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ለመሣተፍ የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት ማረጋገጫ መስጠት እና የፕሮፌሽናል ስኪልስ እና ፋይናንሻል ሊተርሲ ዎርክሾፕ መከታተል እንደሚኖርብኝ ። የስልጠናው ዝርዝር በኢ-ሜይል እንደሚላክልኝ ገብቶኛል።
4. ተገንዝቤአለሁ የሙያዊ ልምድ ወደምሳተፍበት ቦታ እና ከዚያም መልስ የመጓጓዣ ሃላፊነቱ የራሴ መሆኑን። (5 - 8 እድሜ) ያሉ ተማሪዎች በሙሉ በ "Kids Ride Free program" አማካይነት "Ride On"፣ "Ride On Flex" እና አንዳንድ የሜትሮበስ የጉዞ መስመሮችን ጭምር በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ በ "Youth Cruiser SmarTrip card" በመጠቀም በነጻ ለመጓጓዝ ይችላሉ። በትምህርት ቤትህ(ሽ) እና በሌሎች ጣቢያዎችም ለ SmarTrip cards ማመልከቻዎች ይገኛሉ። Youth Cruiser SmarTrip card እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ለበለጠ መረጃ፣ ይህንን የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት ድረ-ገጽ ይጎብኙ፦ www.montgomerycountymd.gov/DOT-Transit/kidsridefree/። ለሥራ ልምድ ምደባ የሚደረገው ከራሴ ፍላጎት ጋር በተጣጣመ መልኩ እና እንደቦታው መገኘት የሚወሰን መሆኑን እገነዘባለሁ።
5. ተረድቻለሁ ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ወቅታዊ መረጃዎች በኢ-ሜይል ስለሚላኩልኝ ከሠመር ራይዝ ጽ/ቤት-Summer RISE office ካሳወቁኝ በኋላ የግሌንም ሆነ የ MCPS ኢ-ሜይሎቼን በየቀኑ ማየት እንዳለብኝ።
6. ተገንዝቤአለሁ የሥራ ልምድ ከማገኝበት ድርጅት ጋር የራሴን መርሃግብር የማቀናጀት ሃላፊነት እንዳለብኝ ።
7. ተስማምቻለሁ ጥሩ የመከታተል ልምድ፣ ስነምግባር፣ ትክክለኛነት፣ ቅደምተከተልን መጠበቅ፣ የተባለውን ሠዓት መጠበቅ፣ ብስለት፣ ተገቢ አለባበስ፣ እና አግባብነት ያለው የቢዝነስ ባህርይና ደንቦችን ማክበር/ማሳየት እንደሚኖርብኝ። የሥራ ልምድ በምወስድበት ድርጅት/Career Experience Host አማካይነት ሊቃለል የማይችል ማንኛውም ጉዳይ ወይም ስጋት ቢያጋጥመኝ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤትን-MCPS Summer RISE Program office በ summer-rise@mcpsmd.org ወይም የስልክ ቁጥር 240-740-5599 በመደወል እገናኛለሁ።
8. ገብቶኛል የሥራ ልምድ የሚሰጠኝ ድርጅት ተጨማሪ የምልመላ መስፈርቶች ሊኖረው እንደሚችል። ማንኛውም የሚፈለግብኝ ተጨማሪ የምልመላ መስፈርት ቢኖር የሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ከሚጀመርበት ከጁላይ 6 አስቀድሞ የሥራ ልምድ ከማገኝበት ድርጅት ጋር በቀጥታ የማስተካከል ኃላፊነት አለብኝ።
9. ተረድቻለሁ የሥራ ልምድ ለሚሰጠኝ ድርጅት/my Career Experience Host ተቀጣሪ አለመሆኔን። የሥራ ልምድ የሚሰጠኝ ድርጅት/My Career Experience Host ከሠመር ራይዝ ተሳታፊዎች ወዲያውኑ የሚያገኘው ምንም አይነት ጥቅም አይኖርም፣ እናም አንዳንዴ ሥራቸው እንኳ ሊደናቀፍ ይችላል። የሙያ ልምምድ በሚሰጠኝ ድርጅት/my Career Experience Host የእለት ተእለት ሥራ ውስጥ (ፋይል ማድረግ፣ ሌሎች የጽሕፈት ሥራዎችን ማከናወን፣ ወይም ደንበኞችን መርዳት) በመሣሠሉት ተግባሮች በመደበኛነትም ሆነ ወይም በተከታታይ በቀጥታ እንደማልሰማራ ተገንዝቤያለሁ። የሙያ ልምምድ የሚሰጠኝ ድርጅት/my Career Experience Host ስለ ቢዝነሱ/ድርጅቱ አጠቃላይ የሆኑ መግለጫዎችን ይሰጠኛል እና ስለ ቢዝነሱ/ድርጅቱ ሚናዎች፣ ኃላፊነቶች፣ እና ተግባሮች ትምህርት ይሰጠኛል። ሥራ አስፈጻሚው(ዋ) ወይም ማኔጀር ዉጤታማ በሆነ መንገድ ለመከወን የሚረዳ ጥራት፣ ክህሎቶች፣ እና እውቀትን በጥልቀት በመሻት እነዚህን ተግባራት እፈጽማለሁ። በበርካታ የሥራ ቅጥር አካባቢዎች ላይ መጠቀም የምችለዉን ሙያዎች ለመማር እድል ይኖረኛል።
10. ተስማምቻለሁ በየሣምንቱ ከሠመር ራይዝ ፕሮግራም ያገኙሁትን ልምድ እና በፕሮግራሙ መጨረሻ የሚኖረኝን አስተያየት ዳሰሳ ሞልቼ ማቅረብ እደሚኖርብኝ/my Summer RISE Program experience።
11. ተገንዝቤያለሁ እና ተስማምቻለሁ/IT IS AGREED AND UNDERSTOOD የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች/Summer RISE Program participants በውጤታማነት ካጠናቀቁ በኋላ ለፕሮግራም ወጪአቸው እንደ ማካካሻ አበል የሚቆጠር $300 በኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ክፍያ ይደረጋል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ካጠናቀቅሁ በኋላ MCPS የእኔን ስም (first and last name) ለ "Educational Systems Federal Credit Union" ይሰጣል። ከባንክ ድርጅት ጋር በፊት የተከፈተ አካውንት ከሌለኝ፣ በ Educational Systems Federal Credit Union ወይም ሌላ የምመርጠው ባንክ ላይ አካውንት የመክፈት እድል ይኖረኛል። አበሉን ለማግኘት በአካል በምሳተፍበት "professional skills and financial literacy workshop" አውደጥናት ላይ የቀጥታ ገንዘብ ማስገቢያ ቅጽ ማቅረብ ይጠበቅብኛል። የባንክ አካውንት ለመክፈት የተለየ ሁኔታ ካጋጠመኝ፣ የእኔን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት "College and Career Information Coordinator" አነጋግራለሁ ወይም የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤትን/Summer RISE Program office በ summer-rise@mcpsmd.org ወይም በስልክ ቁጥር 240-740-5599 በመደወል አነጋግራለሁ።

12. ***ተገንዝቤአለሁ*** በሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program በመሣተፌ የሥራ ልምድ በሚሰጠኝ ድርጅት ተቀጣሪ እንደማያደርገኝ፣ እና በሰራተኛነት ለመቀጠር መጠበቅ እንደማይኖርብኝ።

13. ***ገብቶኛል/I UNDERSTAND*** ቪድኦ ሪኮርድ እደረግ ይሆናል፣ ፎተግራፍ እነሣ ይሆናል፣ እና/ወይም በሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ላይ ባለሁበት ወቅት የሆነ ጊዜ ላይ ሪኮርድ እንደምደረግ። እነዚህ ምስሎች እና/ወይም ሪኮርዶች ስለ ሠመር ራይዝ "Summer RISE" ለማስተዋወቅ እና ምስሎቹ ያለተጨማሪ መግለጫ ለተለያዩ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተስማምቻለሁ። በእነዚህ አጠቃቀሞች ምክንያት ምንም ክፊያ እንደማይሰጠኝ እና ምስሎቹ፣ ቪድዎች፣ ሪኮርዶቹ፣ እንዲሁም ማናቸውም በዚህ መነሻ ምክንያት የሚፈጠሩ ሥራዎች ባለቤትነቱ የ MCPS መሆኑን እገነዘባለሁ።

14. ***ገብቶኛል/I UNDERSTAND*** የሥራ ልምድ የሚሰጠኝ ድርጅት/Career Experience Host የእኔን የሥራ ልምድ ተሳትፎ በሚመለከት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጋር መረጃ እንደሚለዋወጥ። የሥራ ልምድ የሚሰጠው ድርጅት/Career Experience Host ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ከማንም ሌላ ሦስተኛ ወገን ጋር መረጃ አይለዋወጥም።

15. ***ተገንዝቤያለሁ*** ይህንን ስምምነት፣ ወይም የ Career Experience Host ደንቦች እና መመሪያዎችን ባላከብር፣ ወይም ሌሎች ማናቸውንም የ Summer RISE Program ደንቦችን ማክበር ካልቻልኩ፣ ከሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program እንደምወገድ እና $300 አበል ለማግኘት እንደማልችል።

16. ***ምንም አይነት አሳሳቢ ነገር ቢኖረኝ*** ስለ ሥራ ልምድ፣ ወደ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤት በፍጥነት ሪፖርት መደረግ ያለበት summer-rise@mcpsmd.org ወይም በስልክ ቁጥር 240-740-5599 ነዉ።

ስለ "Summer RISE 2020 Student Agreement" የተማሪ ስምምነት ለማመልከት በመመዝገቢያ ቅጽ/ፎርም ላይ ባለዉ ሳጥን ላይ ምልክት እንዲያደርጉ ይገለጻል፣ እናም ይህ በኤክትሮኒክ የምታቀርበ(ቢ)ው ስምምነት እና የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ከግል ፊርማህ(ሽ) ጋር እኩል ተመጣጣኝ መሆኑን እንደተገነዘብክ(ሽ) ይቆጠራል።